www.abyssinialaw.com

# የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሀገ- መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ መንግስት ማፅደቂያ አዋጅ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ሀገ መንግሥቱን ስለማሻሻል

ጳጉሜ 5 ቀን 1987 የፀደቀው የክልሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ መንግስት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## 3. ስለ ነባር ህጎች ተፈጻሚነት

በስራ ላይ ያሉ ህጎች ከተሻሻለው ሀገ-መንግሥት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 4. ሕገ-መንግሥቱ በስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሀገ-መንግሥት ከመስከረም 30/1997 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት

ፕሬዝዳንት

# መግቢያ

እኛ የሐረሪ ህዝብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሲደርስባቸው የነበረውን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ባህላዊ ኃይማኖታዊ ጭቆና ጫናና ተጽእኖ በተለያየ ስልት መልክና ቦታ ሲታገሉ ቆይተው በመጨረሻ በግንቦት ወር 1983 ለዚሁ ሁሉ ምክንያት የሆነውን ሥርዓት በማያዳግም ሁኔታ ለመጣል በመቻሉ በተለይ ጭቁን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ታሪካቸው ባህላቸውና ቋንቋቸውን ለማዳበር በአጠቃላይ ብሔራዊ ህልውናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩንና ይህም ህዳር 29 ቀን 1987 በኢትዮጵያ ህዝቦች በጸደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት መረጋገጡን በመገንዘብ፣

የሐረሪ ህዝብ ምንም እንኳ በምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳድር፣ በራሱ ታሪክ ወግና ባህል ይኮራ የነበረ ቢሆንም በ1886 ዓ.ም በተደረገበት ወረራ በነፍጠኛው ሥርዓት ሥር ከመውደቁም በላይ ይህንን ስርዓት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት ለእስራትና ብሎም ለስደት በመዳረጉ በራሱ ክልል በቁጥር አናሳ መሆኑ የተነሳ ልዩ አወካከል ስልት ማስፈለጉን በመረዳት፣

የሐረሪ ሕዝብ ሲደርስበት የነበረውን ግፍና ጭቆና ሲከፋሉ ከነበሩት ከአካባቢው የኦሮሞ ህዝብ እና ከሌሎች የክልሉ ነዋሪ ህዝቦች በመሆን የክልሉን አስተዳደር በጋራ ማቋቋምና መምራት ያለባቸው መሆኑን በማመን፣

በክልላችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የማለሰብና የብሔር ብሔረሰብ መሠረታዊ መብቶች የተከበሩበትና ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ አመለካከትና ግንኙነት በማረምና በማስተካከል መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተለይም እኛ የሐረሪ፣ የኦሮሞና ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ፍትሐዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር በተለይም ሦስቱን የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልና በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት በግልፅ ማስቀመጥና ተጠያቂነታቸውንም በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

**በዚሁ መሰረት እኛ <u>የሐ</u>ረሪ ክልል ምክር ቤት አባላት የመረጠንን ህዝብ በመወከል ከዚህ በፊት ተመክሮበት የጸደቀውንና በስራ ላይ ያለውን የክልሉን ህገ መንግሥት በጥልቀት ተመልክተን ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ የቀረበውን ህገ መንግሥት መክረንበትና ተወያይተንበት ዛሬ መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ አጽድቀነዋል፡፡**

## ምዕራፍ 1

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ተብሎ የሚጠራ ዲሞክራሲያዊ መዋቅር ያለው መንግሥት በዚህ ህገ-መንግሥት ተመስርቷል፡፡

### አንቀጽ 2

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ግዛት ወሰን

የሐረሪ ሕዝብ ክልል በሰሜን በኮምቦልቻና በጃርሶ ወረዳዎች በምስራቅ በጉርሱምና በባቢሌ ወረዳዎች በደቡብ በፌዲስ ወረዳና በምእራብ በአለማያ ወረዳ የሚዋሰን ነው፡፡

## አንቀጽ 3

## ሰንደቅ ዓላማና አርማ

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ይኖረዋል። ሰንደቅ ዓላማውም መደቡ ነጭ ሆኖ ከላይኛው በርዝ ገባ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ ቀይ መስመር ሲኖረው ከታችኛው በርዝ ከፍ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ አረንጓዴ መስመር ይኖረዋል። በቀዩና በአረንጓዴው መስመር መካከል ዓርማ ይኖረዋል።
2. የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት የሚያስተላልፉት መልዕክት፤
   ሀ. ነጩ መደብ የክልሉ ሕዝብ በፍትህና በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ ሰላም ያለውን ስሜትና ፍላጎት ያመለክታል፤
   ለ. ቀዩ መስመር ሕዝቡ ለመብቱና ለነጻነቱ ያደረገውን ትግልና የከፈለውን መስዋዕትነት ያመለክታል፤
   ሐ. አረንጓዴው መስመር ሕዝቡ ለልማትና ለዕድገት ቆርጦ መነሳቱንና የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ያመለክታል።

## አንቀጽ 4

## የክልሉ መዝሙር

የሐረሪ ክልል ሕዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲሁም የተገኘውን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንጸባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል። ዝርዝሩን በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 5

## ርዕሰ ከተማ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ርዕሰ ከተማ ሐረር ነው።

## አንቀጽ 6

## የስራ ቋንቋ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የስራ ቋንቋ ሐረሪ እና ኦሮምኛ ናቸው።

## አንቀጽ 7

## የፆታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

# ምዕራፍ ሁለት

# የህገ-መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

## አንቀጽ 8

## የህዝቡ የስልጣን ባለቤትነት

www.abyssinialaw.com

የሐረሪ ሕዝብ [illegible] ባለቤት ሲሆን የህዝቡ የባለቤትነትም የሚገለጸው በዚህ ህገ መንግሥት መሰረት በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በሚያደርገው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

## አንቀጽ 9

## የሕገ-መንግሥት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡

1. ይህ ህገ መንግሥት የክልሉ የበላይ ህግ ነው። ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሠራር ወይም የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ የመንግሥት አካል የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህን ህገ-መንግሥት የማክበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።
3. በዚህ ህገ-መንግሥት ከተደነገገው ውጪ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 10

## ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ______ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።
2. በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀጽ 11

## የመንግሥትና የሀይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

## አንቀጽ 12

## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለህዝቡ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3. ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች

### አንቀጽ 13

### ተፈጻሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪ, የሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ የተካተቱ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕጋጋት፣ ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ብቶች ስምምነቶችና ከሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተመጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ፡፡

## ክፍል አንድ

## ሰብዓዊ መብቶች

### አንቀጽ 14

### የሕይወት የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገረሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነት መብትና፣ ነጻነት አለው፡፡

### አንቀጽ 15

### በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም፡፡

### አንቀጽ 16

### የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

### አንቀጽ 17

### የነጻነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነጻነቱን አያጣም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

### አንቀጽ 18

www.abyssinialaw.com

### ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከል

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም፡፡ በማንኛውም ዓላማና ሁኔታ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውም ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ማሟላት የሚለው" ሀረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፡-
   ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሰራ የተወሰነን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራውን ማንኛውም ሥራ፣
   ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትኩ የሚሰጠው አገልግሎት፣
   ሐ. የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ የሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማነኛውም አገልግሎት፣
   መ. በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀምን ማነኛውም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ሥራ፣

### አንቀጽ 19

### የተያዘ ሰዉ መብት

1. ማንኛውም ሰው ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ በሚያዝበት ጊዜ የቀረበበት ክስና የተያዘበት ምክንያት በሚገባው ቋንቋ እንዲነገረው መብት አለው፡፡
2. የተያዘ ሰው የተከሰሰበትን ጉዳይ በተመለከተ ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ ለመናገር ከመረጠ ደግሞ የሚሰጠው ቃል በፍርድ ቤት በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠው መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም የተያዘ ሰው በተያዘ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ



www.abyssinialaw.com

ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው:: ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ማምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም::

ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበ በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለው::

4. የያዘው አካል ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነጻነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው:: ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል:: ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚወስነው ኃላፊ የሆኑት ሕግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት በሚያስከብር መልኩ መሆን አለበት::

5. ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም:: በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም::

6. የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው:: ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሰረት ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፈታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል::

## አንቀጽ 20

## የተከሰሰ ሰዉ መብት

1. የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝቡ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው:: ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታ ወይም የአገሪቱን ወይም የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክር በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል::

2. የተከሰሰ ሰው ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረውና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አለው::

3. ማንኛውም [illegible] ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንዲጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለው:: በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለው::

4. የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበው እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለው::

5. የተከሰሰ ሰው በመረጠው የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም ከሌለውና ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ካጋጠመ ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለው::

6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠበት ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ተከሳሽ ቅሬታ ካለው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል::

7. ተከሳሽ የፍርዱ ሂደት በማይገባው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለው::

## አንቀጽ 21

## በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ መብት

1. በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው ሰብዓዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለው::

2. ማንኛውም የታሰረ ሰው ከትዳር ጓደኛው፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ ከኃይማኖት አማካሪዎቹ፣ ከሐኪሞቹና ከሕግ አማካሪዎቹ ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኙት እድል የማግኘት መብት አለው::

## አንቀጽ 22

## የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም:: እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ በነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም::

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም

www.abyssinialaw.com

ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

## አንቀጽ 23

### በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግና ሥነ ሥርዓት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም::

## አንቀጽ 24

### የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው::
2. ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው::
3. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለው::

## አንቀጽ 25

### የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፣ በመካከላቸው ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል:: በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ በማንኛውም አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ዜጎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው::

## አንቀጽ 26

### የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱና ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው:: ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል::
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፍባቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም::
3. የመንግሥት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው:: አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነት፣ የሕዝቡን ሰላም ለመጠበቅ፣ ወንጀል ለመከላከል፣ ጤናንና የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር ዓላማዎች በወጡ ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም::

## አንቀጽ 27

### የኃይማኖት የሕሊናና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የኃይማኖት ነፃነት አለው:: ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ኃይማኖት ወይም ዕምነት የመያዝ ወይም የመቀበል እና የኃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ ወይም የመግለፅ፣ መብትን ያካትታል::
2. በፌዴራል ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 90/2/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የኃይማኖት ተከታዮች ኃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የኃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ::
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላው ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም::
4. ወላጆችና ሌሎች ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የኃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው::
5. ኃይማኖትንና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደኅንነት፣ ሰላምን፣ ትምህርትን፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና መንግሥት ከኃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል::

## አንቀጽ 28

### በሰብእና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ

## አንቀጽ 34

## የጋብቻ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነ የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሠረታል፡፡

3. ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ሲሆን ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡

4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በኃይማኖት በባህል ሥርዓቶች ላይ ተመሥርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡

5. ይህ ሕገ-መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፍቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 35

## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ-መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው፡፡

2. ሴቶች በዚህ ሕገ-መንግሥት በተደነገገው መሠረት ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡

4. ሴቶች ከጎጂ ባህል ተፅዕኖ የመላቀቅ መብታቸው መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡ ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው

www.abyssinialaw.com

[illegible] ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡

5. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች፡-

ሀ/ የወሊድ ፍቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፣ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

ለ/ የወሊድ ፍቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት፣ ከሙሉ የደሞዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡

6. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች እቅድና በፕሮጀክት ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ ማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ውርሱን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡

8. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡

9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 36

## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት

ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች

የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት በጤናውና

በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠሩ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፡

ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን::

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀዳሚነት መታሰብ አለበት::

3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው::

4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ህጻናት ጋር እኩል መብት አላቸው::

5. መንግሥት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል:: በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል::

## አንቀጽ 37

## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው::

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፡

ሀ/ ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፡

ለ/ ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው::

## አንቀጽ 38

## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማናቸውም የክልሉ ሕዝብ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት::

www.abyssinialaw.com
[illegible] ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፡

ለ/ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሠረት የመምረጥ፡

ሐ/ በዚሕ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 33 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት ሲሞላው መመረጥ፡

መ/ ምርጫው ሁሉ አቀፍ፡ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልፅበት ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ በሐገሪቱን ሕገ-መንግሥትና በምርጫ ሕግ መሠረት መሆን አለበት::

2. ማንኛውም ሰው በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለመሳተፍ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈፀማሉ::

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የሕዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

## አንቀጽ 39

## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብቶች

የሐረሪ ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው:: በዚህ መሠረት የሐረሪ ሕዝብ፡

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብ የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀም፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ መብት አለው::

2. በራሱ መልክአ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የማከናወን ራሱን የመስተዳደር እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ውስጥ በነፃነትና አድልዎ በሌለበት ተገቢና ፍትሃዊ [illegible] ውጤታማ ተሣትፎ [illegible] መብት አለው፡

www.abyssinialaw.com

3. ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ በራሱ መልክአ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት አለው።

4. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር /1/ /2/ እና /3/ የተጠቀሱት መብቶች ታግደ፣ ተረግጦ፣ ወይም ተሸራርፏ ብሎ ባመነበትና እንኙህም መብቶች በኢፌዴሪ መንግስት አንድነት ጥላ ሥር ሆኖ ሊያስተካከላቸው ባልቻለበት ጊዜ እስከ መገንጠል ድረስ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል፡

5. የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በሥራ ላይ የሚውለው፡

ሀ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፡

ለ/ የጉባኤው የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፌዴራሉ መንግሥት ሕዝብ ውሳኔ ሲያደራጅ፡

ሐ/የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፡

መ/ የፌደራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለጠየቀው ለሐረሪ ሕዝብ ስልጣኑን ሲያስረክብና፡

ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. በዚህ ህገ መንግሥት ውስጥ «የሐረሪ ህዝብ» ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑና የስነ ልቦና አንድነት ያላቸው በተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖር ህብረተሰብ ማለት ነው።

## አንቀጽ 40

## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ይከበርላታል። ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ/የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ «የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው ማኅበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ ፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና ተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።

3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው።

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው። አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል።

5. የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

6. ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።

7. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት አለው።

2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

www.abyssinialaw.com

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።

4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

5. የክልሉ መንግሥት አካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

6. የክልሉ መንግሥት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከታተላል፣ እንዲሁም በሚካሄደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የስራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

8. መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 42

## የሠራተኞች መብት

1. ሀ/ የፋብሪካ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል።

ለ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው።

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት እውቅና ባገኙ መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።

መ/ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

3. እነዚህ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት ሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋምበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ።

## አንቀጽ 43

## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል።

## አንቀጽ 44

## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።

2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዛወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

## ምዕራፍ አራት

## የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል

## አንቀጽ 45

## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት በክልል እና በቀበሌ የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር መዋቅሮች ሊያዋቅርና ሥልጣንና ተግባራቸውን ሊወስን ይችላል።

www.abyssinialaw.com

2 ሐረር ከተማ የራስ አስተዳደር ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

### አንቀጽ 46

### የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1 የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አውጪ አካል የሐረሪ ክልል ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው::

2 የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው::

3 የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው::

### አንቀጽ 47

### የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌደራሉ መንግሥት ወይም ለፌደራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ይሆናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግሥት:-

2.1. የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል::

2.2. የክልሉን ህገ መንግሥትና ሌሎች ህጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል::

2.3. የፌደራል መንግሥት በሚያወጣው ህግ መሰረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል::

2.4. ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያቋቁራል:: የህግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትና ይህንን ህገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል::

2.5. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል::

[illegible] ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል::

2.7. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 28 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆነው በህግ መሰረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል::

2.8 ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል::

2.9. በክልሉ መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል::

2.10. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል::

2.11. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል::

2.12. በክልሉ በግል ባለቤትነት ስር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል::

2.13. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ከሚገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ የስራ ግብርና የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይሰበስባል::

2.14. ከፌደራሉ መንግሥት ጋር

ሀ/ በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ ሥራ ግብር፣ የሽታጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል::

ለ/ ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለ አክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል::

ሐ/ ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሰረት ይካፈላል::

2.15 በክልሉ መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፍቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል::

2.16 ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል::

2.17 በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል::

### ምዕራፍ አምስት

### የክልሉ ም/ቤት አወቃቀርና፣ አወካከል ሥልጣንና ተግባር

## አንቀጽ 48

### የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት 36 አባላት ያሉትና በሁለት ጉባኤዎች የተዋቀረ የክልል ም/ቤት ነዉ::

## አንቀጽ 49

### የም/ቤቱ ጉባኤዎች

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ሁለት ጉባኤዎች:-

ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና

ለ/ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ናቸዉ::

2. የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 50/1/ እንደተመለከተዉ የሚወከሉ ሃያ ሁለት አባላት ይኖሩታል::

3. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 50 /2/ እንደተመለከተዉ የሚወከሉ 14 የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይኖሩታል::

## አንቀጽ 50

### የጉባኤዎች አከፋፈል አወካከልና አመራረጥ

1. የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ አባላት በሁለት የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ አባላት ያሉት ጉባኤ ነዉ::

አወካከሉ:-

ሀ/ ከጀገል ምርጫ ክልል 4 አባላትና

ለ/ ከጀገል ዉጭ ካሉት የከተማ ቀበሌዎችና የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራትን የሚያጠቃልል የምርጫ ክልል 18 አባላት ይመረጣል::

2. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በክልሉ ዉስጥና ከክልሉ ዉጭ በሌላ በኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል::

3. የጉባኤዉ አባላት ምርጫ ነፃና ቀጥተኛ በሆነ ድምፅ በሚስጥር በመስጠት ስርዓት ይፈጸማል::

## ክፍል አንድ

## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

## አንቀጽ 51

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በጋራ የሚሰበሰቡበት ም/ቤት ነዉ:: በዚህ ህገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ህግ አዉጪና

www.abyssinialaw.com ይ
የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነዉ::

2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ/ የክልሉን ሕገ-መንግስትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል::

ለ/ በዚህ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79 በተደነገገዉ መሠረት የክልሉን ሕገ-መንግስት ያሻሽላል::

ሐ/ የፌዴራል ሕገ-መንግስት ለክልሎች የተሰጠዉን ስልጣን በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል::

መ/ ለክልሉ ፕሬዝደንትነት በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ጠቋሚነት የሚቀርበዉን እጩ በ2/3ኛ ድምጽ መርምሮ ይመርጣል::

ሠ/ የክልሉን የዉስጥ አስተዳደር ያዋቅራል ያደራጃል::

ረ/ የክልሉን የሕዝብ ደህንነትና ፀጥታን በሚመለከት ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል::

ሰ/ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤና በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት የሚቀርቡለትን አዋጆች ደንቦች መመሪያዎችና ፖሊሲዎች መርምሮ ያፀድቃል::

ሸ/ በክልሉ ፕሬዝዳንት የቀረቡትን ም/ፕሬዝዳንት፣ የክልል አስፈፃሚ/ካብኔ/ አባል የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸዉን ኃላፊዎች ሹመት ያፀድቃል::

ቀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝደንት ምክትል ፕሬዝደንትና ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር ይሾማል::

በ/ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚቀርቡትን ዳኞች ሹመት ያፀድቃል::

ተ/ የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ ያወጣል::

ቸ/ ለክልሉ በተሰጠዉ የገቢ ምንጭ ወሰን ግብርና ታክስ ይጥላል::

ነ/ የክልሉን አመታዊ በጀት ያፀድቃል::

ኘ/ በክልሉ ዉስጥ ማናቸዉም ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያዉጃል::

አ/ የክልሉን መንግሥት የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጎች ያወጣል::

ወ/ በህጉ መሰረት ምህረት ያደርጋል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል::

ዐ/ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ

www.abyssinialaw.com

ይጠራል፣ የአስፈጻሚውን አካል አ... ይመረምራል::

## አንቀጽ 52

### የም/ቤቱ አመራርና አሠራር

1. ም/ቤቱ የራሱ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይኖሩታል::
2. እንደአስፈላጊነቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይኖሩታል::
3. አፈ-ጉባኤው በህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በኩል እንዲሁም ምክትል አፈ-ጉባኤ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በኩል ቀርበው በምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምፅ ይመረጣሉ::

## አንቀጽ 53

### የአፈ-ጉባኤዉ ስልጣንና ተግባር

1. የም/ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል::
2. የም/ቤቱን ጠቅላላ ሥራዎች ያስተዳድራል::
3. በም/ቤቱ አባላት ላይ የሚወሰኑ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ያስፈጽማል::
4. የአፈ-ጉባኤው ሌሎች ሥራዎች በዝርዝር የሚወጣ ሌላ ሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 54

### የምክትል አፈ-ጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

1. በአፈ-ጉባኤ ተለይቶ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::
2. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## አንቀጽ 55

### የም/ቤቱ አባላት መብትና ግዴታ

1. ማንኛውም የም/ቤቱ አባል በም/ቤቱ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም::
2. ማንኛውም የም/ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ም/ቤቱ ፍቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም::
3. ማንኛውም የም/ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ከም/ቤት አባልነት ይወገዳል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 56

### የም/ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. ... መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል::
2. የም/ቤቱ አባላት የሥራ ዘመን ለአምስት አመት ነው:: የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል:: የቀድሞው ም/ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲስ ም/ቤት ሥራውን ይጀምራል::
3. የም/ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል:: የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤት አባላት መካከል ከ1/3ኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠሩ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::
4. የም/ቤቱ ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል:: ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በአባላቱ ወይም በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ከተጠየቀና ከም/ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል::

## አንቀጽ 57

### የዉሳኔ አሰጣጥና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶች

1. ከም/ቤት አባላት መካከል ከ2/3ኛ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::
2. ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈው በም/ቤቱ ስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይሆናል::
3. ምክር ቤቱ አሰራሩንና የሕግ አወጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ዝርዝር ሕጎችን ሊያወጣ ይችላል::

## ክፍል ሁለት

### የጉባኤዎች ስልጣንና ተግባር

## አንቀጽ 58

### የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤ በክልሉ ም/ቤት ከሚኖረው ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂ በተመለከተ ረቂቅ ሕግ ያመነጫል፣ ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያጸድቃል::
2. የግብርና ታክስ አዋጆችን ያመነጫል፣ ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያጸድቃል::

3. የክልሉን በጀት ገምግሞ ለክ www.abyssinialaw.com ም/ቤት ያቀርባል:

4. በክልሉ የም/ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባኤነት አንድ አባል ይጠቀማል::

5. የጉባኤዉን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና

6. ቃለ ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል::

## አንቀጽ 59

## የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ብሔረሰብ ቋንቋና ባሕል በሚመለከት ፖሊሲና ሕግ ያወጣል::

2. በክልሉ ዉስጥ የሐረሪ ብሔረሰብ ታሪክና ባሕል የሚያንጸባርቁ ቅርፃቅርፆች የመቃብር ቦታዎች የመስኪድና የአድባራት አጠባበቅን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል::

3. የሐረሪ ብሔረሰብ በፌዴራል መንግስት የፌድሬሽን ም/ቤት በሚወክሉ ወይም የሚወክሉ አባል ወይም አባላትን ይመርጣል::

4. የክልሉን ፕሬዝዳንትና የም/ቤቱን ምክትል አፈ-ጉባኤ ይጠቁማል::

5. የጉባኤዉን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል ጉባኤና

6. የጉባኤዉን ቃለ ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል::

7. የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በዚህ ህገ መንግስት አንቀጽ 39 መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል::

## ምዕራፍ ስድስት

## የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት

## አንቀጽ 60

## ስለ አስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ስልጣን የተሰጠዉ ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ነዉ::

2. የመስተዳደሩ ም/ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚሰጡት ዉሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ::

## አንቀጽ 61

## የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት አባላት

1. የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ፕሬዝዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዝዳንቱ፣ የቢሮ ኃላፊዎችና የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሚወስናቸዉ ... ካል ነዉ::

2. ፕሬዝደንቱና የክልሉ አስፈፃሚ አካላት በዚህ ህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች የሚሰጣቸዉ ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል::

3. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ሰብሳቢ ፕሬዝደንቱ ይሆናሉ::

4. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ይሆናል::

## አንቀጽ 62

## የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በፌዴራል ሕገ-መንግስት የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል::

1. በፌዴራል መንግስት፣ በክልሉ ምክር ቤት እና በሐረሪ ጉባኤ የወጡት ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸዉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል::

2. የክልሉን የመስተዳደር አካላትና ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል::

3. የክልሉን ማሕበራዊ ዕድገትና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን
• የሚያስችሉ ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል::

4. የክልሉን መስተዳደር ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል::

5. የክልሉን ቢሮዎችና አስፈፃሚ አካላት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል::

6. ህግና ስርአት በክልሉ መከበሩን ያረጋግጣል::

7. የልማት፣ የማህበራዊ ጉዳይ ጸጥታና ደህንነትን በሚመለከት የህግና የፖሊሲ ረቂቆችን ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በስራ ላይ ያዉላል፣

8. በክልሉ ም/ቤት በሚሰጠዉ ስልጣን መሰረት ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል::

9. ስለ ስራዉ እንቅስቃሴ ለክልሉ ም/ቤት ሪፖርት ያቀርባል::

10. በምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል::

www.abyssinialaw.com

11 በዚህ ሕገ መንግስት መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል::

12 በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን በሕግ ሊያቋቋር ይችላል::

## አንቀጽ 63

## የፕሬዝዳንቱ አሰያየም

1. ፕሬዝዳንቱ በሀረሪ ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ በም/ቤት የሚመረጥ ይሆናል::
2. የፕሬዝዳንቱ የስራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የስራ ዘመን ይሆናል::
3. ፕሬዝዳንቱ በምክር ቤቱ ፊትለፊት ቃለመሀላ መፈጸም ይኖርበታል:: የቃለመሀላው ይዘት እንደሚከተለው ይሆናል::

«እኔ _____ በዛሬው ዕለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ሃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁኝ»

## አንቀጽ 64

## የፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል::

ለ/ የክልሉ ም/ቤት የሐረሪ ጉባኤ እና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚያወጧቸውን ህጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከታተላል፣ ያስፈፅማል::

ሐ/ የክልሉን ም/ፕሬዝዳንት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንቱን፣ ዋና ኦዲተር፣ ም/ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር፣ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላትና ሌሎች የክልሉ መስሪያ ቤቶች ሀላፊዎችን ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያሾማል::

መ/ በንዑስ አንቀጽ /ሐ/ ሥር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ም/ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ሃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል::

ሠ/ ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጪ የሆኑ ሃላፊዎች ም/ቢሮ ሃላፊዎች ኮሚሽነሮችና ሌሎች የሥራ ሃላፊዎችን ይሾማል::

ረ/ የካቢኔ አባላት፣ የቢሮ ሃላፊዎች ወይም የጽ/ቤት ሃላፊዎች ችግር ስኖርባቸው በማገድና ለክልሉ ም/ቤት በማቅረብ ያስወግዳል::

ሰ/ የዜሐረዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ህግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ሀይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል::

ሸ/ በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖችን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል::

## አንቀጽ 65

## የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት

ፕሬዝዳንቱ በዚህ ህገ መንግስትና በሌሎች ሕጎች የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

## አንቀጽ 66

## የምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

ሀ. በክልሉ ፕሬዝዳንትና በክልል መስተዳድር ም/ቤት የሚሰጡት ተግባራትን ያከናውናል::

ለ/ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል::

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ስልጣን

## አንቀጽ 67

## ስለ ነጻ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነጻ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ-መንግስት ተቋቁሟል::
2. የዳኝነት ስልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግና በህግ የተደነገገውን የዳኝነት ስርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም::

## አንቀጽ 68

## ስለ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ዳኝነት

1. የሀይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በሚወጣ ዝርዝር ህግ መሰረት ሊቋቋሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጣቸው ይችላል::
2. ይህ ህገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት ዕውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሀይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ህገ መንግሥት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ::

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 69

## የዳኝነት ስልጣን

1 የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

2 በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተጽእኖ ነጻ ነው።

3 ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፡ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።

4 ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ስራው አይነሳም።

ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲ.ሲ.ፕ.ሊ.ን ህግ መሰረት ጥፋት ፈፅሟል ወይም ጉልህ የሆነ የስራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፡

ለ/ በህመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፡

ሐ/ የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ አብላጫ ድምጽ ተደግፎ ሲጸድቅ።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አንድን ዳኛ ከዳኝነት ስራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈፅሟል ብሎ ጉባኤው ካመነበት ጉዳዩ በክልሉ ም/ቤት እስኪወሰን ድረስ ከዳኝነት ስራው ይታገዳል።

6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀጽ 70

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይደራጃል።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ስልጣን፡

ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣንና፡

ሐ/ ማንኛውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3 የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከክልላዊ ስልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል።

4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል።

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል።

6. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ም/ቤት አቅርቦ ያስወስናል፡ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።

7. የክልሉ ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች በውክልና ለሚሰሩት ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ከፌዴራል መንግስት የበጀት ማካካሻ ይሰጣቸዋል።

## አንቀጽ 71

## የዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሮዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በክልሉ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።

3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዕጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀውን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የዕጩ ዳኞች ሹመት ያፀድቃል።

## አንቀጽ 72

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምጽ የሚጠከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።

2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 73

### ህገ መንግሥቱን ስለመተርጎም

1. የህገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን ውሳኔ ያገኛል፡፡

2. የህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚስዮን የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ህገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3. የህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት የሐረሪ ተወካይ ሰብሳቢ

ለ/ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሐረሪ ክልል ተወካዮች መካከል አንደኛው ምክትል ሰብሳቢ ሁለተኛው ፀሐፊ ሆነው በኮሚሲዮኑ ይመረጣሉ፡፡

ሐ/ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሐረሪ ጉባኤና በሐረሪ ህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ከእያንዳንዱ ጉባኤ የሚወከሉ ሁለት ሁለት ተወካዮች አባላት፡፡

መ/ የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቀድሞ ፕሬዝዳንት/ፕሬዝዳንቶች/ ድምጽ ሳይሰጡ የሚሳተፉበት፡፡

## አንቀጽ 74

### የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ-መንግሥት ተቋቁሟል፡፡

2. የክልሉ ሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡

3. አባላቱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ...........ሰብሳቢ፤

ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ...........ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ/ በክልሉ መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፤

መ/ በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል የሚሰየሙ 3 ተወካዮች፤

3. የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

ሀ/ የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ህገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ህገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

ለ/ በክልሉ ህግ አውጪ አካል የሚወጡ ህጎች ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለህገ መንግሥት ተርጓሚው ኮሚሲዮን ያቀርባል፡፡

ሐ/ በፍርድ ቤቶች የህገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ

1. ህገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል በአጣሪው ጉባኤ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፡፡

መ/ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለህገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## አንቀጽ 75

### ስለቀበሌ አስተዳደር መቋቋም

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግሥታዊ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል

ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት፤

ለ/ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፤

ሐ/ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ናቸው፡፡

3. የቀበሌ መስተዳድር አካላት አደረጃጀትና ሥልጣንና ሃላፊነታቸውን በተመለከተ በዝርዝር ህግ ይወጣል፡፡



www.abyssinialaw.com

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 76

### የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

1 ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት እና ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ ቁጥር 11 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ያወጣል::

2. የመስተዳድር ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ አፈ-ጉባኤው ምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ማስጸደቅ አለበት::

3. የመስተዳድር ምክር ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል:: ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ ሊታደስ ይችላል::

4. የመስተዳደሩ ምክር ቤት እና ም/ቤቱ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 14፣ 16፣ 18//1/ እና 2፣ 21/1/፣ 24፣ 1/25፣ 27/1/ እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም::

5. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል:: ቦርዱ በፌደራሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 93 /6/ የተጠቀሱት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

### አንቀጽ 77

### የክልሉ ፖሊሲ ዓላማዎች

ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌደራሉንና የክልሉን ሕገ-መንግሥት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በስራ ላይ ሲያውል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ምዕራፍ 10 አንቀጽ 85 እስከ አንቀጽ 92 የተመለከቱትን ብሔራዊ ፖሊሲ [illegible] መሰረት በማድረግ ነው::

### አንቀጽ 78

### የክልሉ ዋና ኦዲተር

1 የክልሉ ዋና ኦዲተር በመስተዳድሩ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል::

2 የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉን ቢሮዎችና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልሉ መንግሥት የተመደበው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ እንዲሰሩ ለተወሰኑ ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለክልል ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል::

3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል::

### አንቀጽ 79

### የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብን ስለማመንጨትና ስለማሻሻል

1. የዚህ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ 3 ድንጋጌዎች በፌደራል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 105 ከተደነገገው ውጭ ሊሻሻሉ አይችልም::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት:-

ሀ/ የህገ መንግሥቱ የማሻሻያ ሐሳብ ከሁለቱ ጉባኤዎች ቢያንስ በአንዱ ሲነሳ

ለ/ የማሻሻያ ሃሳቡ በሁለቱም ጉባዔዎች ለየብቻቸው ውይይት ተደርጎበት ከእያንዳንዱ ጉባኤ በ2/3 ድምፅ ሲደገፍ እና

ሐ/ የክልሉ ምክር ቤት ማሻሻያውን በ2/3 ድምፅ ሲያጸድቅ ብቻ ነው::

### አንቀጽ 80

### ሕገ-መንግሥቱ የሚታተምባቸው ቋንቋዎች

ይህ ሕገ-መንግሥት በሐረሪ፣ በኦሮምኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ይታተማል:: በሐረሪኛ በኦሮምኛ ቋንቋዎች መካከል የትርጉም ልዩነት ሲኖርም የአማርኛው ቅጂ ተቀባይነት ይኖረዋል::